# ምሁር ማነው?

ከመምህር ታደሰ ሽምብራ

ሰሞኑን በፓል ቶክ እያለ የሚፅፈው በልጂግ አሊ ወደ ፓል ቶክ ብቅ አልክ አይበለኝና ባለፈው በአንድ ፓል ቶክ ዶክተር አበባ ፈቃደ ስለ ምሁር ምንነትና ማንነት በሚገባ ስለገለፁ ይህም ለሚከተለው ፅሁፌ መንደርደሪያ ሊሆነኝ በቃ:: ምሁር በእርግጥ ማነው? በሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ምሁር ሊባል የሚገባው ማነው? ወደዚህ ዝርዝር ከመግባቴ በፊት ምሁር ወይም ኢንቴሌክችዋል የሚለው ቃል ከየትና መቸ እንደመጣ ማየቱ ቢጠቅምም ቢዘህ ላይ በስፋት አላትትም::

ኢንቴሌክችዋል ወይም ምሁር የሚለው ቃል ዛሬ በምንረዳው መልኩ በሀያኛው ክፍለ ዘመን የመጣ ነው ማለት ይቻላል:::: ይህን ፅንሰ ሀሳብ በማዳበር ደረጃ ከግራ ክንፍ ሆነው ከፃፉት ብዙ ጊዜ የሚጠቀሰው አንቶኒዮ ግራምቺ ሲሆን ትራዲሺናልና ኦርጋኒክ በሚል ምሁሮችን ለይቷቸዋል:: ትራዲሺናል ወይ የ "ዱሮ" የሚላቸው ሀቅና ምርምርን እንጂ መደብና ፖለቲካን አንፈልግም የሚሉ ናቸው:: ትስስራቸው ግን ካለው ስርዓትና ስልጣን ጋር መሆኑ/ በሀሳብም ደረጃ/ ተጠቅሷል:: ኦርጋኒክ የሚባሉት ደግሞ ከሰራተኛው መደብ ጋር ወይም ሰፊው ሕዝብ ከሚባለው ጋር የተሳሰሩና ለዚሁ መደብም የሚቆረቆሩትን ነው:: በመደብ ትግል ውስጥ ቦታቸውን ከህዝብ ጎን የሚይዙ የሚወግኑ ናቸው ማለት ነው:: ከግራምቺ ቀጥሎ ከግራ ሳይሆን ከቀኝ ስለ ምሁር ማንነት የፃፉ አሉ--ለምሳሌ ሚሼል ፉኮ ምሁርን የገለፀው በስራውና ከ "ሀቅ ፖለቲካ" ጋር ባለው ግንኙነት ነው:: ፉኮ ሀቅን በስልጣን ላይ ወይም የበላይነትን ከያዘው ሀይል ውጪ ለመያዝ ለመገንዘብ መቻልን ከምሁሩ ጋር ያያይዘዋል:: ምሁሩ ከጋራ ሀቅ ጋር መቆራኘትም የለበት ባይ ነበር:: ከመደብ አቀዋምና ፖለቲካ "መራቅ" ወይም ክሪቲካል ዲስታንስ መያዝ የሚለውም አመለካከት በዚሁ ጊዜ የመጣ ነው:: ምሁሩ ከፍጭቱ ርቆ ይገኝ የሚለውን በዘመናችን እነ ኖአም ቾምስኪና ሚቹ ኤድዋርድ ሳይድ በተግባርም በፅሁፍም ፉርሽ አድርገውታል::

ተማሪዎች በነበርን ጊዜ ምሁር ማለት የፈረንጁን ትምህርት /አስኮላ/ ያካሄደ ያገባደደው ነበር:: እንግሊዝኛ መናገር ነበር ስልጣኔ ወይ የአዋቂ መለያ:: ዶሮ እንኳን ከተለቀ የፈረንጅ ዶሮ የሚባልበት ዘመን ነበር:: ዘመናዊነትና ምሁርነት ከሀገር ጋር የተያያዘ ሳይሆን ከሀገር ባህልና ክብር ጋር የተጣላ ነበር ማለትም ይቻላል:: ምሁር ሲባል በሀገር ዕውቀትና ቅርስ የዳበረ ሳይሆን፤ቅኔ ያመ ድጓን ያወቀው ሳይሆን፤ የሀገር ታሪክን ያወቀው ሳይሆን፤ የሐጅ ዩሱፍና የሐረርን- የይፋትን ታሪክ ያወቀውን ሳይሆን፤ ወዘተ ምሁር የሚባለው የባዕዳን ስልጣኔንና ታሪክ አወቅኩ ያለው፤ ዲፕሎም ዲግሪ ያዝኩ ያለውና ዶክተር ፕሮፌሰር ተባልኩ ብሎ ካባ አልብሱኝ--ጎንበስ ጎንበስ በሉልኝ ባዩ ሆኖ ይገኛል:: ማነው ምሁር ስንል እንግዲህ ዶክተር አበባ ሊያሳስቡ እንደሞከሩት የሀገርን ጥቅም አስቀድመው የሚቆሙትን ሀገር ወዳድ ምሁሮችን፤ ዕውቀታቸው በሀገር ላይ የተመሰረተ መሆኑ ላይ ጫና ሰጥተን ማየት አለብን ማለት ነው:: አንድ የፖለቲካ ቀልደኛ ከዓመታት በፊት የወያኔ ፖሊሶች ሮንድ ሲዞሩ ሶስት የሚሆኑት ሁለቱ ማንበብና መፃፍ በመቻላቸው ሶስተኛው እነዚህን " አደገኛ ምሁሮች" የሚከታተል ነው ብሎ ነበር:: ማንበብ መፃፍ የ ለ ነው ወይ ምሁር? እንግሊዝኛ መናገር የማይችል ምሁር አይደለም ማለት ነው? የባዕድ ወይም የፈረንጁ ኮራኩር (ይህ የወያኔ ቃል ነው

ሎሌ ወይም መሳሪያ ለማለት) ካልተሆነ ምሁር መባል አይቻልም? የሀገራችን ታላቅ ሰው ኮለኔል አስናቀ እንግዳ በአንድ ስብሰባ ምሁር ማለት ለሀገሩ የሚቆምና ለሕዝብ ጠበቃ የሚሆነው ነው ብለው ነበር:: ወይም ሀይሉ ገብረ ዮሐንስ እንዳሉት አንደበት ለሌለው አንደበት የሚሆኑት ናቸው:: ደሀው ይናገራል ብለው፤በረከተ መርገም ብለው ኡኡ የሚሉ ማለት ነው:: የተማራችሁ ናችሁና ስራ ሞልቷል እየተባሉ ይህን ድለላ አንሰማም ብለው ድሀው ይማር፤መሬት ለአራሹ ብለው ለሕዝብ መጮሁን የመረጡት በእርግጥም ምሁር ነበሩ:: ከዚያም ለጭቁኑ ሕዝብ ሲሉ ዕውቀታቸውን ብቻ ሳይሆን ህይወታቸውንም የለገሱትን ምሁሮች በእርግጥም ያስታውሷል::

በሀሳብ ዓለም፤ በምርምር፤ በስነ ፅሁፍ ወዘተ የተሰማሩትን ሁሉ በደፈናው ምሁር ማለት ሲቻል የሀገሩን ታሪካዊ ቅርስ ቦታ ያልሰጠና ዕውቀትና ስልጣኔን ከባዕድ ጋር ብቻ ያያዘን በምሁር ደረጃ መመደቡ ቢያንስ አከራካሪ ነው:: ሱፍ መልበስ፤ ስለ ያሬደ ሳይወሳ ስለ ሞዛርትና ቢትሆቨን መራቀቁ፤ ዘርዓያዕቆብን ንቆ ስለ ስፒኖዛ መፈላሰፉ፤ የሀገርን ቋንቋ ናቅ ናቅ ማድረጉና የሀገርን ባህል ማጣጣሉ፤ ፈረንጅ አምላኩ መሆን በአጠቃላይ ምሁር ሊያሰኝ አይገባውም:: ዛሬ የትምህርት ደረጃና ይዘት ወድቆ ባለበት ደግሞ ምሁር ነኝ የሚለው ተማርኩ የሚለውንስ ጠንቅቆ አውቆታል ወይ የሚለውን ጥያቄ ያስነሳል:: ትምህርት ራሱ ለምን ወደሚለው መኳተናችን ደግሞ የሚመለጥ ጉዞ አይደለም:: ገጣሚዎቹ ካሉት ዘረፍ ላድርግና ከፊታደ አዘዘ “ለመደንቆር አልማርም” ግጥም የተወሰኑ ስንኞችን ላቅርብ--

“ መማር ለመሸሽ ለመደበቅ
አልጋ ስር ገብቶ
ትንፋሽ ቀብሮ ልሳን ዘግቶ
አንገት ሰብሮ ጉልበት ደፍቶ
“ብልሀት ስትራተጂ” እያሉ
ለዘለዓለሙ መማቀቁ::

መማር ለመፍራት
ዐይኑን ሲያፈርጠው በእቶን እሳት
ፊቱን ሲያጋየው በቋያ እሳት
“ቆይ አውቆ አይመስለኝም” ለማለት
ሌላይቱን እስኪደግማት::
መማር አሁንም ለመፍራት
“ኑሮ በዘዴ” እያሉ
ኑሮን በስቃይ ለመገንባት::”

ገጣሚው ይህን ብሎ ሲደመድም ደግሞ ምሁርነት ፍርሀት በሆነባቸው ላይ ተበሳጭቶ....

“አዎ! እንዲህ ከሆነ ለምንም
ለሚማሩትም አዝ ለሁ፤እኔስ በቃኝ አልማርም
መማር መደንቆር ከሆነ ፤እንዲሁ ልደንቁረው
እኔስ በቃኝ አልማርም፤ትምህርት ለእኔ ጠላቴ ነው

አልማርም፡፡
በቃኝ እኔስ አልማርም፡፡”

ለፈቃደ አዘዘ የትምህርት ዋጋና ምሁርነት ነፍስን ከወራዳ መወሻሻያ ቦታ ከማራቅና ከድፍረት ጋር አልፎም ከህዝባዊነት ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ገጣሚ ህማ ቱማ ደግሞ “ይቅርብኝ መማሩ” በተሰኘው ግጥሙ ይህንኑ መልዕክት በራሱ መንገድ አቅርቦታል፡፡

“ መማር ከሆነማ አንጎል ደፍኖ መኖር
ማወቅ ከሆነማ ህሊና ቢስ መሆን
መንቃት ከሆነማ ዓይን ገልጦ መኘታ
መብሰል ከሆነማ የደደቦች ታርጋ
መማር ከሆነማ ሀገር ወገን ሽጦ
ሰብዕናን መቅሰፍ ማንነትን ክዶ
ማወቅ ከሆነማ እነ እንቶኔን መሆን
ለጠባቦች መንጋ በሎሌነት አድሮ
በወገን መጨከን
በሀገር መጨከን
ይቅርብኝ ልደንቁር ይቅረ ባልማረው
ተማረ የተባው ሰው መሆን ካቃተው፡፡”

በዚህ መልክ ምሁርነትን ወይም ትምህርት ራሱን መረዳት ይገባል ካልን ምሁር ልንለው የምንችለው ትምህርት ቤት ገብቶ ዲፐሎማና ዲግሪ የሰበሰበውን ሳይሆን ለሀገሩና ለህዝብ ፈፍቅር ያለውንና ዕውቀቱን ሊያውል የተነሳውን ነው ማለት ነው፡፡ ሀገር ትጣራላች ብለው ከትምህርት ገበታ ተነስተው ወደ ትግሉ የገቡትና ፈቃደ እንዳለው ኑሮ በዘዴ ብለው፤ከመሞት መበርከት ብለው “አንገት ደፋ ድምፅን ጠፋ” በሚል መርህ የተማሩትና ዲግሪ የሰበሰቡት የላቁ ምህሮች ሊባሉ አይችልም፡፡ ህሊናን የገደለ ምሁርነት ስለሆነ ከሕዝብ ዕይታ አንፃር በድንቁርናም ሊፈረጅ ይችላልና ነው፡፡ በእርግጥ ከህብረተሰቡ ነባራዊና ተጨባጭ ሁኔታ ውጪ በደፈናው ዩኒቨርስቲና ኮሌጅን በር ያለፈ ሁሉ ምሁር ይባል ማለት ይቻላል፡፡ ይህ ግን ትክክል አይሆንም፡፡ ከይዘቱ ወይም ተልዕኮው ጋር ገላጭ ቅፅል ካላከልንበት፡፡ ደደብ ምሁር ማለቱም ይሰራል፡፡ ሆዳም ምሁርም እንዲሁ፡፡ የወያኔ ምሁርም ማለት ይቻላል፡፡ ከሕዝቡና ከሀገር ምሁር ለመለየት ማለት ነው፡፡ ለዲግሪማ ለገሰ ዜናዊም ከአንግሊዝ ተልኮለታል፡፡ እንድርያስ እሸቴም ፕሮፌሰር ነው፡፡ ስንቱን ወጣት ያስጨረሰው ግርማ ብሩም ተምሯል፡፡ ህፃናትን ሳይቀር የጨፈጨፈው አሳዝነው ባይሳም የኮርኔል ኒውዮርክ ምሩቅ ነበር፡፡ የተማረ ህዝባዊ ምሁር ከሆነ ለሀገር ቤዛ ይሆናል፡፡ የተማረ በሆዱ ከተገዛ ህሊናው ላይ ከተኛ ደግሞ ሀገርን የሚያዋርድና የሚያጠፋ ይሆናል፡፡ ለመለስ ዜናዊ ያደሩ ምሁራን ተብዬዎች ሁሉ በሕዝብ ምሁር የሚባሉ አይደሉም፡፡ ከሀዲዎች እንጂ፡፡

ተማርን ብለው ዛሬ በሕዝብ ላይ የሚኩራሩት ሁሉ፤ አንድ ፀሀፊ ነገደ ቬራተን ያላቸው ጉዶች፤ የህሊና ዓይናቸውን ሆዳቸው የጋረደባቸው መከረኞች፤ ዶክተር ፕሮፌሰር ተብዬዎች ሰልፋቸው ከሕዝብና ከሀገር ጋር እስካልሆነ ድረስ “ተማሩ ወይ?” ለሚለው ጥያቄ ቀለም ነድተዋል ግን ተደናቆሩ የሚለው መልስ ተገቢ ይሆናል፡፡ የእናት ሆድ ዝ ጉርጉር ነው ለማለት ባዕድን መጥቀስ የማወቅ

ምልክት አይደለም:::: የሀገራችን ምሳሌዎችና ተረቶች፤ መፅሀፍት ወዘተ ዕውቀትን ያዘሉ ናቸው:: በሀገሩ የሚኩራራ (ይህ ወደ ትምክህት እስካልሄደ ድረስ) ጤነኛ ነው:: ለዚህም ነው ዶክተር አበባ  የሀገርና ሕዝብን ቅርስና ክብር ከመጨበጥና ከማንፀባረቅ አንፃር ምሁርን ሊገልጡ የሞከሩት:: በዋሺንግተን ዲሲ ባሉ ራዲዮ ጣቢያዎች የሚሰሙ ጥራዝ ነጠቅ አንግሊዝኛና ከአማርኛ ደባላቂ ንግግሮች አንድ ምሳሌ ናቸው:: መራቀቅን ሳይሆን ውድቀትን ይጠቁማሉና:: በቅርቡ በአንድ ድህረ ገፅ ላይ አንድ ግለሰብ በታገሉት ምሁሮች ላይ የጭቃ ጅራፉን ያወርዳል:: ግለሰቡ በትግሉ መስክ የት ተሰልፎ እንደነበር ግልፅ ባይሆንም ምሁሮችን በምርጥነት “ኤሊት” በሚል ሊፈረጅ መነሳቱ ራሱ ችግሩን ያጋልጥበታል:: ምሁርነት ምርጥነት አይደለም:: ሀገርን ለማዳን ህይወት የለገሱትን በማክበር ፈንታ ለማብጠልጠል መጣሩም የሚያስገምት ይሆናል:: የፖለቲከውን መድረክ ስናየው ተማርን አወቅን ባዮች አጨናንቀውት እየተፎካከሩ ናቸው:: መሪ አታጋይ አዲስ ሀሳብ ያቀርባሉ ወይስ እጅ እጅ ያለውን የባንድነት መፈክር በአዲስ ቃል ጠቅለው ዋጡልን ይላሉ? ዶክተር ፕሮፌሰር የምትለዋን ለጠፍ ያደረገ ሁሉ የፖለቲካ አቡን ነኝ እያለ ነው:: ስንመረምረው ግን ሲከፍቱት ተልባ እየሆነ አስቸግሯል:: በትግሉ መስክ ሕዝብ ምሁር ነን መሪ ነን ያሉትን ቀድሟቸዋል:: መሪዎቹ ከፊት ሳይሆን ከወደ ጀርባ ናቸው:: ምሁር ነን አውቀናል ያሉት የትግሉ ሀ ሁ ጠፍቷቸው ገዢው ቡድን ባኣራ ቁጥር ብርክ ይይዛቸዋል:: ሳሩን እንጂ ገደሉን ማየቱ ይሳናቸዋል:: ድንቄም ምሁር!

ማንም በሀገራችን ትምህርት የቀሰመ ሰው ለዚህ የበቃው በሕዝብ ላብ ነው:: ለሕዝብ የሚከፍለው ዕዳ አለበት:: ምሁርነት ቅንነትና እውነተኛትን ያዝላል:: ዕዳን ክዶ ሕዝብን ክዶ መገኘት ዕውቀት ሳይሆን ድንቁርና ነው:: የሀገረን ታሪክ፤ባህልና ቅርስ አንኳሶ ጥሎ ለባዕዱ መወድስ ማቅረብም እንዲሁ ቅሌት ነው:: ህዝባችንን ማክበር አለብን፤ፍረሃታችንን ማሸነፍ አለብን ማለት ነው:: ስርየት ያለው በቆረፈዱ እጆች መዳፍ ውስጥ ነው:: ፈቃደ እንዳለው

“ መማር ቅንጣት ያህል ላይለወጡ
ጉድፍ ከሀገር ዓይን ላያወጡ
እንዲያው ለመኖር ብቻ
በምግብና መጠጡ
በዳግማዊ ልደት ፍልስፍና ፀጉር እየሰነጠቁ::”

ሀገራችን ኢትዮጵያን ከሆዳም ምሁሮች መቅስፍት በትግል እንጠብቃት!!